# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መንግሥት
# THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

# የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
# ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

## መመርያ ስድስት
## *DIRECTIVE SIX*

**የልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት መቋቋም**
**RESPONSES TO ACCIDENTAL RELEASE OF MODIFIED ORGANISM**

**አዲስ አበባ**
**ጥር** 2000

**ADDIS ABABA**
**January 2008**

# መመሪያ ቁጥር 6

## የልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት መቋቋምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ልውጥ ሕያዋን በድንገት ወደ አካባቢ ቢለቀቁ ፈጣንና ቀጥተኛ የመቋቋምያ እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ስለዚህ በደህንነተ ህይወት አዋጅ ቁጥር ……. አንቀፅ 22 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

### 1. ሥያሜ

ይህ መመሪያ «የልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት መቋቋምን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 06/2001» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

# DIRECTIVE No. SIX

**A DIRECTIVE ISSUED TO DETERMINE RESPONSES TO ACCIDENTAL RELEASES OF MODIFIED ORGANISM**

WHEREAS it is essential to give a prompt and direct response to any accidental release of modified organisms,

THEREFORE, this directive is issued in accordance with Article 22 of the Biosafety Proclamation No. ----------------------------

**1. Designation**

This directive may be cited as 'Directive No. 06/ 2009' issued to determine responses to accidental releases of modified organisms".

## 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ለገበያ ማቅረብ» ማለት ልውጥ ሕያውን ለተጤነ ልቀት ለማዋል ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነትን ከተቀበሉ በኋላ በእርዳታ ምግብነት መስጠትን ጨምሮ ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው::

2. «ልውጥ ሕያው» ማለት ሰው ሠራሽ የሆነ፣ ወይም ከሌላ ሕያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደአዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረመል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ስለተከተተበት የዘረመሎች ይዘቱ ወይም የባሕርዩ ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው::

3. «መሥራት» ማለት በዘመናዊ ጥበበ ሕይወት ልውጥ ሕያው እንዲገኝ ማድረግ ነው::

4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

5. «ባለሥልጣን» ማለት በአዋጅ ቁጥር 295/1995 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው::

6. «ተቆጣጣሪ» ማለት የደህንነተ ህይወት አዋጅ፣ በስሩ የወጣ ማንኛውም ደንብና ወይም መመሪያ መከበሩን ለማረጋገጥ የፍተሻና ሌላ የቁጥጥር እርምጃ እንዲወስድ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሾመ ሰው ነው::

7. «አመልካች» ማለት የሚጠይቀውን ዕንቅስቃሴ ለማካሄድ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ ያመለከተ ሰው ነው::

8. «እንቅስቃሴ» ማለት ልውጥ ሕያውን መሥራትን፤ ወይም ለትምህርት፣ ለምርምር፣ ለምርት፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት፣ ወደ ውጪ ለመላክ፣ በትራንዚት ለማስተላለፍ፣ ለተጤነ ልቀት፣ በዝግ አጠቃቀም ለማምረት፣ ለማጓጓዝ፣ ለገበያ ለማቅረብ፣ ለሰው ወይም ለእንስሳ በመድኃኒትነት ለመጠቀም፣ ለምግብነት፣ ለመኖነት ወይም ለፋብሪካ ጥሬ ዕቃነት ማዋል፤ ነው::

## 1. Definitions

For the purpose of this Proclamation:

1. ‘Placing on the market’ means obtaining an advance informed agreement for deliberate release or making available to third parties a modified organism for any use by selling, giving away or in any other way, and includes giving as aid food.
2. ‘Modified organism’ means any biological entity which has been artificially synthesized, or in which the genetic material or the expression of any of its traits has been changed by the introduction of any foreign gene or any other chemical whether taken from another organism, from a fossil organism or artificially synthesized.
3. ‘Making’ means the development of a modified organism through modern biotechnology;
4. 'Person' includes any natural or juridical person.
5. 'Authority' means the Environmental Protection Authority of the Federal Democratic Republic of Ethiopia established pursuant to Proclamation No. 295/2002.
6. ‘Inspector’ means a person appointed pursuant to the directives issued by the Authority to undertake examination and any other control measures to ensure compliance with the proclamation on biosafety regulations or directives issued under it.
7. **‘**Applicant**’** means any person who submits an application to the Authority seeking an advance informed agreement to be engaged in a transaction.
8. **'**Transaction' means any making or use of any modified organism in teaching, research, production, import, export, transit, deliberate release, production under contained use, transport, placing on the market, or use as a pharmaceutical, as food, as feed or for processing.

9. «ዝግ አጠቃቀም» ማለት በሰው ወይም በእንሰሳት ጤና ወይም በአካባቢ ላይ የሚከተል ያልታቀደ ተፅዕኖን ለመከላከል ከልውጥ ሕያዋን ጋራ የተያያዘ ጠንቅን የመቋቋምያ ስልት አተገባበርን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 03/2001 እንደ ሁኔታው በዓንቀፅ 4.8 ወይም 4.9 እንደተዘረዘረው በቁሳዊና በንጥረ ነገራዊ ከለላ ታጥረው ልውጥ ሕያዋን እንዲሰሩ፣ እንዲያድጉ፣ እንዲከማቹ፣ እንዲወገዱ ወይም ትምህርትንና ምርምርን ጨምሮ በሆነ ሌላ መንገድ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው።

10. «የተጤነ ልቀት» ማለት ከግንዛቤ በመነጨ ስምምነት መሰረት ልውጥ ሕያውን ለንግድ፣ ለምግብ፣ ለእርዳታ ምግብ፣ አካባቢን ለማፅዳት፣ ለማስተማሪያነት፣ ለምርምር፣ ለመስተዋት ቤት፣ ለውሃ ውስጥ እርባታ፣ ለእንስሳት መኖ፣ ለሰው ወይም ለእንስሳት ህክምና ወይም ለሌላ ጥቅም በማዋል ወደ አካባቢ እንዲዳረስ ማድረግ ነው።

11. «ጠንቅ» ማለት ከየቱኛውም እንቅስቃሴ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ፣ በአጭር፣ በመካከለኛ ወይም በረጅም ጊዜ በሰው ወይም በእንስሳ ጤና፣ በብዝሐ ሕይወት፣ በአካባቢ፣ በማህበረሰቦች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወይም ባህላዊ ሁኔታ ወይም በአገሪቷ ኢኮኖሚ፣ ላይ ሊከተል የሚችል አደጋ ነው።

12. «ፕሮቶኮል» ማለት በአዋጅ ቁጥር 362/1995 የፀደቀው የብዝሐ ሕይወት ኮንቬንሽኑ የካርታኼና የደሕንነተ ሕይወት ፕሮቶኮል ነው።

9. ‘Contained use’ means any operation in which modified organisms are made, grown, stored, destroyed or used in any other way including for teaching and research isolated by physical and chemical barriers as specified in Articles 4.8 or 4.9 of Directive no. 03/2009 issued to determine the procedures of a risk management strategy for dealing with accidents involving modified organisms, as the case may be, with a view to effectively preventing their contact with, and their unintended impact on, humans, animals or the external environment.

10. ‘Deliberate release’ means any introduction into the environment of a modified organism based on an advance informed agreement and includes, *inter alia*, any use in commerce, food, aid food, remediation, teaching, research, greenhouses, aqua-culture, animal feed or other inputs for animals, medicines for humans or animals, or disposal.

11. ‘Risk’ means direct or indirect, short, medium or long-term danger that may befall human or animal health, biological diversity, the environment, socio-economic or cultural conditions of local communities or the economic condition of the country from any transaction.

12. ‘Protocol’ means the Cartagena Protocol on Biosafety to the Convention on Biological Diversity ratified through Proclamation No 362/2003.

## 3. መመርያው ተፈፃሚ ስለሚሆንባቸው እንቅስቃሴዎች

ይህ መመርያ ለተጤነ ልቀት በባለሥልጣኑ ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ባልተሰጠበት በማንኛውም ልውጥ ሕያው ማንኛውም እንቅስቃሴ ሲካሄድ በሚገጥም ያልተጤነ ልቀትና በተያያዙ አደጋዎች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## 4. በአደጋ ጊዜ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

4.1 ማንኛውንም የልውጥ ሕያው ድንገተኛ ልቀትን ለመቋቋም እንዲቻል ያልተጤነ ልቀት መቋቋሚያ ቡድንን እንዲሰይምለት ባለስልጣኑ የአካባቢ ምክር ቤት ሰብሳቢውን ይጠይቃል፡፡

4.2 የአካባቢ ምክር ቤት ሰብሳቢው ያልተጤነ ልቀት መቋቋምያ ቡድኑ ሊቀመንበርንና አባላትን ድንገተኛ አደጋን የመቋቋም እርምጃ የመውሰድ አቅም ባላቸው ተቋማት ከሚሰሩ ባለሙያዎች መካከል ይሰይማል፡፡

4.3 ባለስልጣኑ ላልተጤነ ልቀት መቋቋምያ ቡድኑ ፀሐፊ ይመድብለታል፡፡

## 3. Transactions subject to this Directive

This Directive shall apply to any unintended release or any related accident during any transaction.

## 4. Emergency measures

4.1 The Authority shall, in order to be ready to respond to any accidental release of any modified organism, request the Chairperson of the Environmental Council to establish an Accidental Release Response Group.

4.2 The Chairperson of the Environmental Council shall appoint the Chairperson and the members of the Accidental Release Response Group to comprise representatives of institutions capable of undertaking risk management measures.

4.3 The Authority shall appoint a secretary for the Accidental Release Response Group.

4.4 ያልተጤነ ልቀት መቋቋምያ ቡድኑ ተግባራትና ኃላፊነቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፣

ሀ. ብሔራዊ የአደጋ መቋቋምያ እቅድን ማዘጋጀት፣ ሲያስፈልግ መተግበርና በየጊዜው ማሻሻል፣

ለ. ባለሥልጣኑ ለተጤነ ልቀት ከግንዛቤ የመነጨ ስምምነት ባልሰጠባቸው ልውጥ ሕያዋን በሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ወቅት ያልተጤነ ልቀትንና ሌሎች አደጋዎችን ለመከታተልና ለመዘገብ የሚያስችሉ ተገቢ ስርዓቶችን መዘርጋት፣

ሐ. ከልውጥ ሕያዋን ያልተጤነ ልቀት ሊመጣ የሚችለውን በብዝሀ ሕይወት፣ በአካባቢና በሰውና በእንስሳት ጤንነት የሚደርስ አደጋን ለመከላከል የሚየስችል ፈጣን የመቋቋምያ ስልት ምን ጊዜም ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፣

መ. የልውጥ ሕያው ያልተጤነ ልቀት የገጠመ እንደሆነ አካባቢን ይሁን የሰውን ወይም የእንሰሳትን ጤና እንደማይጎዳ ለማድረግ በቂ ዝግጅት ምን ጊዜም መኖሩን ማረጋገጥ፣

ሠ. ወጪዎችን ለማስመለስና ካሳን ለማስከፈል እንዲያግዝ የአደጋ መቋቋምያ እርምጃ በሚወሰድበት ጊዜ የሚደርሱ ወጪዎች በተሟላና በትክክለኛ መንገድ መመዝገባቸውን ማረጋገጥ፣

ረ. ያልተጤነ ልቀትን ለመቋቋም የሚያስችል የሰው ኃይል፣ ገንዘብና መሣርያ ዝግጁ መሆኑን ማረጋገጥ፣

4.5 ማንኛቸውንም ልውጥ ሕያዋንን የሚመለከት አደጋ ሲያጋጥም ለመቋቋም የሚያግዙ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን የመምራት ኃላፊነት ያልተጤነ ልቀት መቋቋምያ ቡድኑ ብቻ ነው::

4.4 The duties and responsibilities of the Accidental Release Response Group shall be to:

a) Develop, implement when needed and keep updating a national risk management plan;

b) Develop appropriate systems for the detection and reporting of accidental releases and other incidents that happen during any transaction involving any modified organisms that have not been cleared for deliberate release through an advanced informed agreement issued by the Authority;

c) Ensure that there is a constant readiness to respond to any accidental release of any modified organism to prevent damage to biodiversity, the environment or human or animal health

d) Ensure that there is a constant readiness for the disposal of modified organisms recovered after accidents without any harm to humans, animals and the environment;

e) Ensure that complete and accurate records of expenditures incurred in responding to any accidental release are maintained so as to facilitate cost recovery and the payment of compensation;

f) Ensure the prompt availability of manpower, financial resources and equipment to deal with any accidental release;

4.5 The Accidental Release Response Group shall be the sole authority responsible for response to any accident involving modified organisms and it shall direct the activities of institutions and individuals that may offer assistance.

4.6 ያልተጤነ ልቀት መቋቋምያ ቡድኑ የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች ለመወጣት እንደአስፈላጊነቱ፣ ሆኖም አነሰ ቢባል በየ6 ወሩ፣ ስብሰባ ያደርጋል፡፡

## 5. የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ _______________ ቀን ______________ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ________________ ቀን _______________ ዓ.ም.

የአካባቢው ምክር ቤት ሰብሳቢ

4.6 The Accidental Release Response Group shall meet at such times and with such frequency as may be necessary to fulfill its duties and responsibilities which, in any event, shall not be less than every six months.

**2. Effective Date**

This directive shall enter into force as of the________ day of 200___

Done at Addis Ababa, this ____________ day of ________200____

Chairperson of the Environmental Council